## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 962/2015

መጋቢት 2015 ዓ.ም

## መመመሪያ ቁጥር 962/2015

## <u>የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 962/2015</u>

በጨዉ ምርት አቅርቦት፣ ስርጭት እና ግብይት ላይ እየታየ ያለዉን ያልተገባ አካሄድ በማስተካከል የአካባቢዉ ህብረተሰብ እና ሀገሪቱ ከዘርፉ ተገቢዉን የኢኮኖሚ ጥቅም እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለህብረተሰቡ ለምግብ ፍጆታ የሚቀርበው ጨው ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ከማምረቻ ቦታ የሚወጣው ጥሬ፣ የታጠበ እና በኬሚካል የተቀነባበረ ጨዉ ለሰዉ ምግብነት እንዳይዉል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጨዉ ምርትን ለምግብ ፍጆታ የሚጠቀመውን ሸማች ከኢፍትሐዊ የንግድ ውድድርና የአቅርቦት እጥረት በመከላከል ለሚከፍለው ዋጋ ጥራቱን የጠበቀ እና በተፈለገው መጠን ምርት እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) እና በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006አንቀጽ46 (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962 /2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ነጋዴ"** ማለት የሙያ ሥራው አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲል በንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሰራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የንግድ ሥራ ተብሎ በህግ የተወሰነውን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤

2. **"የጥሬ ጨው አምራች"** ማለት እንደ አግባቡ ጨው በሚመረትበት ክልል ወይም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል በተሰጠው ፈቃድ መሠረት የጥሬ ጨው ማዕድንን በማምረት የሚያቀርብ ነጋዴ ነው፤

3. **"የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካ"** ማለት የጥሬ ጨው ምርት በሚመረትበት ቦታ ብቻ የሚገኝ ሆኖ፡-

   ሀ/ ጥሬ ጨውን በማጠብ እና በአዮዲን በማበልጸግ እስከ 50 ኪ/ግ ጨው አዮዳይዝድ መሆኑን በሚገልፅ ማሸጊያ አሽጎ በቀጥታ ለሰው ምግብነት ወይም ለምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች በጅምላ ለገበያ የሚያቀርብ፤

   ለ/ ጥሬ ጨውን በማጠብ የታጠበ ጨው መሆኑን በሚገልፅ ማሸጊያ እስከ 50 ኪ.ግ አሽጎ በግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፣

   ሐ/ ጥሬጨው በናፍታሊን በመቀላቀል በናፍታሊን የተቀላቀለ ጥሬ ጨው መሆኑንና ለምግብነት የማይውል እንደሆነ በሚገልፅ ማሸጊያ እስከ 50 ኪ.ግ አሽጎ በግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፣

   መ/ ከውጪ የሚገባውን የገበታ ጨው የሚተካ ወይም ለኤክስፖርት የሚውል ጨው አቀነባብሮ ለገበያ የሚያቀርብ ነው፤

4. **"አነስተኛ የጨው አቀነባባሪ"** ማለት በሀገሪቱ በማንኛውም ስፍራ የሚገኝ ሆኖ በጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች አዮዲን የተቀላቀለበትን ጨው ከጅምላ አከፋፋዮች ወይም ከአቀነባባሪ ፋብሪካዎች በመረከብና በመፍጨት እንዲሁም የታጠበ ጨውን በመፍጨትና ከአዮዲን ጋር በመቀላቀል ከ3 ኪ/ግ ባልበለጠ ማሸጊያ አሽጎ ለገበያ የሚያቀርብ ነጋዴ ነው፤

5. **"የጨው ጅምላ አከፋፋይ"** ማለት ምርቱን ከአቀነባባሪ ፋብሪካዎች በመግዛት ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በማጓጓዝ ለዚሁ ሥራ ባስመዘገበው መጋዘን አከማችቶ ለአነስተኛ አቀነባባሪዎች ወይም ለቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ነጋዴ ነው፤

6. **"ቸርቻሪ"** ማለት ለሰው ምግብነት የሚውለውን በአዮዲን የበለጸገ ጨው ከአቅራቢዎች ወይም ከአከፋፋዮች በመረከብ በቀጥታ ለሸማቾች የሚሸጥ ነጋዴ ነው፤

7. **"የጨው ነጋዴ"** ማለት ከማምረት እስከ ችርቻሮ ንግድ ድረስ ባሉ የጨው ምርት የንግድ ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ እና ምርቱን በየደረጃው ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

8. **"የምግብ ጨው"** ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲውል ታስቦ በአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES 70መሠረት ተዘጋጅቶ የቀረበ በአዮዲን የበለፀገ የጨው ምርት ነው፤

9. **"የታጠበ ጨው"** ማለት ለሰው ጎጂ የሆኑ ባዕድ ነገሮችን ከጥሬ ጨው ውስጥ በማስወገድ በአዮዲን ለማበልጸግ ወይም ለኢንዱስትሪ ግብአትነት ለማዋል ዝግጁ የሆነ ጨው ነው፤

10. **"ናፍታሊን ኬሚካል"**ማለት ለኢንዱስትሪ ግብአትነት የሚቀርብ ሆኖ ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዳይውል ታስቦ ያልታጠበ ጨው ላይ የሚቀላቀል ኬሚካል ነው፤

11. **"የምግብ ኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው"** ማለት በአዮዲን የበለጸገ ጨው ሆኖ የምግብ ምርቶችን በኢንዱስትሪ ለማቀነባበር እንዲያገለግል በ50 ኪ.ግ መያዣ ታሽጎ የሚቀርብ ጨው ነው፤

12. **"የኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው"** ማለት ያልታጠበ ጨው ሆኖ በናፍታሊን ኬሚካል የተቀላቀለ እና ለምግብነት የማይውል እንደሆነ በሚገልፅ ማሸጊያ ታሽጎ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት እንዲውል የሚቀርብ ጨው ነው፤

13. **"የጨው ምርት መግለጫ"** ማለት ሌሎች ዝርዝር የምርት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የታጠበ ጨው፣ በአዮዲን የበለጸገ የምግብ ጨው ወይም ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውል ከናፍታሊን የተቀላቀለ ጨው ስለመሆኑ በማሸጊያው ላይ የሚጻፍ መግለጫ ነው፤

14. **አግባብነት ያለው አካል"** ማለት በክልሎች በየእርከኑ ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት ነው፤

15. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

16. **"የጨው ምርት የሚገኝበት ክልል"** ማለት የጨዉ ማዕድን በተፈጥሮ ሃብትነት የሚገኝበት ክልል ነዉ፤

17. **"ሚኒስቴር"** ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

18. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

19. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ በሚካሄድ ማናቸውም አይነት የጨው ግብይት እና በግብይቱ ተሳታፊ በሆነ **ነጋዴ** ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

4. <u>የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፦

1. ለምግብ ጨው ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውለው የጨው መጠን የአቅርቦት ችግር ሲያጋጥም ቀጥታ ግዢ መፈፀም እንዲቻል የገበያ ትስስር ይፈጥራል፤
2. በማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የሚመረተው እና ለገበያ የሚቀርበው የምግብ ጨው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES 70 ማሟላቱን ይቆጣጠራል፤
3. የታጠበ ጨውን በግብአትነት እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው ኢንዱስትሪዎች ልዩ የጨው ምርት መግለጫ ባለዉ ከረጢት በመረከብ ለታለመለት ዓላማ ብቻ ስለማዋላቸው ይቆጣጠራል፤
4. በየደረጃዉ ያለዉ የጨው ግብይት ይህንን መመሪያ ተከትሎ በፍትሃዊ ውድድር ላይ ተመስርቶ ስለመከናወኑ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

5. የምግብ ጨዉ አቀነባባሪ ፋብሪካዎች የሚያመርቱትን የምግብ ጨዉ ምርት የሚያከፋፍሉላቸው ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴዎችን የሚመርጡበት መስፈርት ግልፅና ህግን የማይቃረን እንዲሁም ሁሉንም አካባቢዎች ያማከለ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
6. የጨው ምርት ነፃ የንግድ እንቅስቃሴን የሚገድቡ ተገቢ ያልሆኑ የኬላ አሠራሮች እንዳይኖሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
7. ለአነስተኛ አቀነባባሪዎች እና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውለው የጨው መጠን አቅርቦት ላይ ችግር ሲያጋጥም እና ከጨው ግብይት ጋር በተያያዘ ቅሬታ እና ጥያቄ ሲቀርብ ምላሽ ይሰጣል፤
8. ለመመሪያው አፈጻጸም የሚረዱ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 5. . <u>አግባብነት ያለው አካል ተግባርና ኃላፊነት</u>

**አግባብነት ያለው አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-**

1. በአዮዲን በልፅገ ለሰው ምግብ ፍጆታ የሚውል ጨው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES 70 አሟልቶ በጨው ምርት መግለጫ ታሽጎ ለገበያ መቅረቡን ይቆጣጠራል፤
2. ምንጩ ያልታወቀ እና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES 70 ያላሟላየጨው ምርት ለገበያ ቀርቦ ሲገኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 6. . <u>የጨው ማዕድን የሚገኝበት ክልል አግባብነት ያለው አካል ተግባርና ኃላፊነት</u>

የጨውማእድን የሚገኝበት ክልል አግባብነት ያለው አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የጥሬ ጨው ምርትን በግብአትነት እንዲጠቀሙ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው የጨው አቀናባሪ ፋብሪካዎች እና ኢንዱስትሪዎች በቂ የጨው ምርት ስለማግኘታቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
2. የጨው አቅርቦት እንዳይስተጓጎል እና ፍትሃዊ ሥርጭት እንዲኖር በክልሉ ካሉ ከሚመለከታቸው ተቋማት እና ከሚኒስቴሩ ጋር በትብብር ይሠራል፤
3. ከማምረቻ ቦታ የሚወጣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውል ያልታጠበ ጨው ለምግብነት እንዳይውል ናፍጣሊ ተቀላቅሎ እና በልዩ ምልክት ባለው መያዣ ታሽጎ መውጣቱን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም ለኢንዱስትሪዎች የሚቀርብ የታጠበ ጨው

ከማምረቻ ቦታ ራሱን በቻለ ለገበያ ማዋል እንደማይቻል በሚገልፅ ከረጢት እየታሸገ መውጣቱን ይቆጣጠራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## በጨው የግብይት ሰንሰለት ተሳታፊ የሆኑ ነጋዴዎች ግዴታዎች

### 7. . የጥሬ ጨው አምራች ግዴታ

**የጥሬ ጨው አምራች** ጥሬ ጨውን በጥራትና በወቅቱ በማምረት የገበያ ትስስር ለተፈጠረላቸው የማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ያቀርባል፡፡

### 8. ጥሬ ጨውን በናፍታሊን የሚቀላቅል አቀነባባሪ ግዴታ

ጥሬ ጨውን በናፍታሊን የሚቀላቅል አቀነባባሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. የጥሬ ጨው ማዕድን በሚገኝበት ክልል ውስጥ ብቻ ጥሬ ጨውን በናፍታሊን ቀላቅሎ ያዘጋጃል፤

2. ያዘጋጀውን ጨው በናፍታሊን የተቀላቀለ፣ ለገበያና ለምግብነት የማይውል’ በሚል ከረጢት ወይም መያዣ ላይ የጨው ምርት መግለጫ ጽሁፍ አዘጋጅቶ በማሸግ ትስስር ለተፈጠረላቸው አከፋፋዮች ወይም አቅራቢዎች ብቻ ለሽያጭ ያቀርባል፡፡

### 9. በናፍታሊን የተቀላቀለ ጥሬ ጨውን ለኢንዱስትሪ የሚያቀርብ አከፋፋይ ወይም አቅራቢ ግዴታ

በናፍታሊን የተቀላቀለ ጥሬ ጨውን ለኢንዱስትሪ የሚያቀርብ አካል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በናፍታሊን ተቀላቅሎ በልዩ ምልክት የተዘጋጀ ጥሬ ጨው ግዢ በመፈጸም ለኢንዱስትሪዎች ያቀርባል፤
2. ምርቱ ለየትኞቹ ኢንዱስትሪዎች እንደተሰራጨ መረጃ ይይዛል፣ ያደራጃል የሚመለከተው አካል ሲጠይቅ ያቀርባል፡፡

### 10 . የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ግዴታ

የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በተፈጠረለት የገበያ ትስስር መሰረት ከጥሬ ጨው አምራቾች ግዢ ይፈጽማል፤
2. ለምግብ ፍጆታነት የሚውለውን በአዮዲን የበለጸገ ጨው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ CES 70 አሟልቶ በቂ እና ተከታታይ በሆነ መጠን ለገበያ ያቀርባል፤
3. በአዮዲን የበለጸገ ጨው በግብአትነት ለሚጠቀሙ የምግብ ኢንዱስትሪዎች እና ለአነስተኛ አቀነባባሪዎች እስከ 50 ኪ.ግ ድረስ የታሸገ ጨው በጅምላ አከፋፋዮችወይም አቅራቢዎች አማካይነት ለገበያ ያቀርባል፤
4. ጥሬ ጨውን በማጠብ ለተፈቀደላቸው ኢንዱስትሪዎችና አነስተኛ አቀነባባሪዎች በቀጥታ ወይም በአከፋፋዮች አማካይነት ያቀርባል፤
5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (4) የተመለከቱት ሶስት ዓይነት የተቀነባበሩ ጨው በየራሳቸው የጨው ምርት መግለጫ ታሽገው እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
6. ግልጽ የመመልመያ መስፈርት በማውጣትና በመመልመል ያቀነባበረውን ጨው በጅምላ የሚያከፋፍሉ ወይም ለኢንዱስትሪዎች የሚያቀርቡ ነጋዴዎችን ይለያል፤

7.በአዮዲን የበለጸገ የጨው ምርት እጥረት እንዳይፈጠር ከማቀነባበሪያ ቦታ ወይም ክልል ውጭ ባስመዘገበው የማከማቻ መጋዘን በጊዜያዊነት መጠባበቂያ ይይዛል፡፡

## 11. <u>የጨው ምርትን በጅምላ የሚያከፋፍል ነጋዴ ግዴታ</u>

የጨው ምርትን በጅምላ የሚያከፋፍል ነጋዴ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. የጨው ምርትን ከአቀነባባሪ ፋብሪካዎች በመግዛት ለአነስተኛ አቀነባባሪዎች ወይም ለቸርቻሪዎች ለሽያጭ ያቀርባል፤
2. በአዮዲን የበለጸገ ጨው በግብዓትነት ለሚጠቀሙ የምግብ ኢንዱስትሪዎች በተፈለገው ጊዜ ለሽያጭ ያቀርባል፤
3. አግባብነት ላለው አካል በማሳወቅ የጨው እጥረት እንዳያጋጥም ለአንድ ወር የሚበቃ ክምችት በመያዝ የተረጋጋ በአዮዲን የበለፀገ ጨው ግብይት እንዲኖር ያመቻቻል፡፡

## 12. <u>የአነስተኛ አቀነባባሪ ግዴታ</u>

**አነስተኛ አቀነባባሪ** ከጨው አቀነባባሪ በቀጥታ ከፋብሪካዎች ወይም ከጅምላ አከፋፋዮች የተረከበውን በአዮዲን የበለፀገ ጨው በመፍጨት ወይም የታጠበ ጨውን በመፍጨትና

በአዮዲን በመቀላቀልእና አስገዳጅ የኢትዮጵያደረጃ CES 70 አሟልቶ እስከ 3 ኪ/ግ በሚደርስ ማሸጊያ በማሸግ ለቸርቻሪ ነጋዴዎች ለሽያጭ ያቀርባል፡፡

13. <u>የጨው ቸርቻሪ ነጋዴ ግዴታ</u>

ጨው ቸርቻሪ ነጋዴ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በአዮዲን የበለጸገ ጨው ከጅምላ አከፋፋዮች ወይም ከአነስተኛ አቀነባባሪዎች በመረከብ በቀጥታ ለሸማቾች ለሽያጭ ያቀርባል፤
2. የምግብ ጨውን ለሸማቾች በማሸጊያው ላይ በተገለጸው የክብደት መጠን ልክ መቅረቡን በማረጋገጥ ሽያጭ ይፈጽማል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14. <u>መረጃ ስለመያዝ</u>

1. ማንኛውም የጨው አቀነባባሪ እና ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴ ስላመረተው ወይም ስላከፋፈለው የጨው ምርት መረጃ በአግባቡ የመያዝና በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡
2. የጨው ምርትን ከማምረቻ ቦታ ውጪ በማንኛውም መንገድ የሚያጓጉዝ አካል ተገቢውን መረጃ የመያዝና በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

15. <u>መረጃን ይፋ ስለማድረግ</u>

በጨው የግብይት ሰንሰለት በየደረጃው ተሳታፊ የሆኑ ነጋዴዎች በህገ-ወጥ ተግባራት ላይ ተሳታፊ ስለመሆናቸው ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ እና አግባብነት ያለው አካል ስለተወሰደባቸው አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

16. <u>ስለተጠያቂነት</u>

1. ማንኛውም የጨው ነጋዴ ይህን መመሪያ ጥሶ ከተገኘ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና አግባብ ባላቸው ሌሎች የሀገሪቱ ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም ነጋዴ ያልሆነ ሰው በምግብ ጨውም ሆነ በኢንዱስትሪ ግብዓት የጨው ምርት ሕገ ወጥ አቅርቦት እና ግብይት እንዲሁም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል መጠን በላይ በማከማቸት ሥራ ላይ ተሳትፎ ከተገኘ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች የሀገሪቱ ሕጐች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ሚኒስቴሩ እና አግባብነት ያለው አካል ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 18. <u>ስለተሻሩ መመሪያዎች እና አሠራሮች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 19. <u>መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከዛሬ መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ

የኢ. ፌ. ዲ. ሪ. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር